# የMY SCHOOL DC ማውጫ



ይማሩ ❖ ያመልክቱ ❖ ይመዝገቡ

MY SCHOOL DC
Learn • Apply • Enroll
MySchoolDC.org

## ለDCPS እና ለቻርተር ትምህርት ቤቶች የዲሲ መደበኛ ማመልከቻ እና ሎተሪ

info.myschooldc@dc.gov
202.888.6336



## MY SCHOOL DC የሚያስፈልገው ማን ነው?

ልጅዎ በ፡ አዲስ ተማሪ የሚሆን ከሆነ የMy School DC ማመልከቻ ያስገቡ።

- ከPK3 እስከ 12ኛ ክፍል ባለው ደረጃ ለሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች፤ ከተማ አቀፍ የሆኑ የ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ
- ከዲሲ ወጣ ብለው በአካባቢው ለሚገኙ ከPK3 አስከ 12ኛ ክፍል ባለው ደረጃ ለሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች፤ ከተማ አቀፍ የDCPS ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ።
- በማንኛውም DCPS ትምህርት ቤት (በወሰንዎ ውስጥ ያለውን ትምህርት ቤት ጨምሮ) የሚሰጡ የPK3 ወይም በPK4 ደረጃ  ፕሮግራሞች፤
- በከተማ ክልል ምርጥ የሆኑ እና ከ9ኛ አስከ 12ኛ ክፍል ባለው ደረጃ ለሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች፤

የሚከተሉት ምክንያቶች ከተከሰቱ ማመልከት አያስፈልግዎትም፤

- ልጅዎ አሁን በሚማርበት ትምህርት ቤት ውስጥ ትምህርቱን የሚቀጥል ከሆነ፤
- ልጅዎ  የDCPS ከK-12ኛ ባለው የትምህርት ክልል ውስጥ ለመማር የሚያዘጋጅ ልዩ ትምህርት እያተከታተለ ከሆነ፤

የ My School DC ምዝገባ ታህሳስ 12 ቀን 2016 ዓ.ም. በ MySchoolDC.org

ድህረ ገጽ ይጀምራል። ማመልከቻው በእንግሊዝኛና በስፓኒሽኛ ቋንቋ ይገኛል።  ስለ ማመልከቻው የሚያብራሩ መመሪያዎች  በአማርኛ፣በቻይንኛ፣በቬትናምኛና በፈረንሳይኛ ተዘጋጅተዋል። በቋንቋዎ እርዳታ ለማግኘት የMy School DC አስቸኳይ መስመር በ(202) 888-6336 ይደውሉ።

የካቲት 1 ቀን 2017 ዓ.ም. | ከ9ኛ አስከ 12ኛ ክፍል ባለው የትምህርት ደረጃ ውስጥ ለመግባት ለሚፈልጉ ተማሪዎች የመጨረሻው የማመልከቻ ማስገቢያ ቀን፤

መጋቢት 1 ቀን 2017 ዓ.ም | ከPK3 - 8ኛ ክፍል የማመልከቻ የመጨረሻ ቀን፤

የሎተሪ ውጤቶች በኦንላይን በMy School DC  የቤተሰብ አካውንት ላይ መጋቢት 31 ቀን 2017 ዓ.ም. ይፋ ይሆናሉ።

### ጥቆማ፤

ጥያቄ አለዎት? የተማሪ ማመልከቻውን ለማዘጋጀት እርዳታ ያስፈልግዎታል? በ MY SCHOOL DC የእርዳታ መስመር በ202-888-6336 በመደወል በሚፈልጉት ዕርዳታ ቋንቋ መጠይቅ ይችላሉ፣ ወይም በኢሜል info.myschooldc@dc.gov በመጠየቅ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።



## ይማሩ

ስለ የህዝብ ትምህርት ቤት ምርጫዎ ለመማር በርካታ መንገዶች አሉ።

- MySchoolDC.org ድህረ ገጽ ይጎብኙ።
  - በክልልዎ ውስጥ ያሉ የDCPS ትምህርት ቤቶችን እና በአቅራቢያዎ ያሉ የህዝብ እና የቻርተር ትምህርት ቤቶችን፣ በአድራሻ ለማግኘት School Finder ይጠቀሙ።
  - በፕሮግራሙ ስለሚካፈሉ ትምህርት ቤቶች ለማወቅ እና የመመዝገቢያ ሰሌዳዎቻቸውን ለማየት የMy School DC ገጽታዎችን ይመልከቱ።
- ስለ ትምህርት ቤቶች ፕሮግራሞች ጥያቄ ካለዎት ትምህርት ቤቶቹን በቀጥታ ይጎብኙ ወይም ስልክ ይደውሉ።
- የሚፈልጉት ትምህርት ቤት የሚማሩ ልጆች ያላቸው ጎረቤቶች ወይም ጓደኞች ጋር ይነጋገሩ እና የትምህርት ቤቶች ዝግጅቶች ላይ ይካፈሉ።
- በሚቀጥለው ገጽ ላይ ያለውን ቅጽ ተጠቅመው የሚያመለክቱባቸውን ትምህርት ቤቶች ዝርዝር ያውጡ። በMy School DC ማመልከቻ እስከ 12 ትምህርት ቤቶች መምረጥ እና በሚፈልጉት ቅደም ተከተል (1ኛ ምርጫ፣ 2ኛ ምርጫ፣ ወዘተ...) ማስቀመጥ ይችላሉ፡

ለእርስዎ እና ለልጅዎ የበለጠ ጠቃሚ የሚሆነውን ያስቡ።

- የትምህርት ቤት ቅርበት ምን ያህል አስፈላጊ ነው እና ልጄን እንዴት አድርጌ ትምህርት ቤት አደርሰዋለሁ?
- ከትምህርት ቤት በፊት እና ከትምህርት በኋላ ትምህርት ለልጄ ምን ያህል አስፈላጊ ነው?
- ለልጄ ምን ዓይነት የትምህርት አካባቢ የተሻለ ነው?
- ለልጄ ምን ዓይነት የትምህርት አሰጣጥ የተሻለ ነው?
- ለልጄ ምን ዓይነት ከትምህርት ውጭ የሚሰጡ ሥርዓተ ትምህርቶች የተሻሉ ናቸው?

በMy School DC የሚካፈሉ ትምህርት ቤቶችን እና ገጽታዎቻቸውን ሙሉ ዝርዝር ለማግኘት MySchoolDC.org ድህረ ገጽን ይጎብኙ ወይም በትምህርት ቤት ወይም በቤተ መጻህፍት የሚገኘውን የMy School DC School ማውጫ ይመልከቱ።

# ይማሩ

ከታች በሚገኘው ሰንጠረዥ ማወቅ የሚፈልጓቸውን ትምህርት ቤቶች ዝርዝር ይጻፉ።  ምርጫዎን ከጨረሱ በኋላ በሚፈልጉት ተራ ተከተል (1ኛ ምርጫዎ፣ 2ኛ ምርጫዎ፣ ወዘተ...) ያስቀምጡ።

| የትምህርት ቤት ስም | የትምህርት ቤት ጉብኝት ቀን | ማስታዎሻዎች<br>ለእርስዎ እና ለልጅዎ በትምህርት ቤት ውስጥ የበለጠ አስፈላጊ ነገር ምንድነው?  የትኛዎቹ ትምህርት ቤቶች ይስማሙዎታል? | ደረጃ |
|---|---|---|---|
| ለምሳሌ፣<br>ትምህርት ቤት ሀለሐ | ጥር 9 ቀን<br>2017 ዓ.ም. | ትምህርት ቤቱ በሳይንስ እና ሂሳብ ላይ ስለሚያተኩር ለልጄ ተስማሚ ነው፤ ሆኖም ትምህርት ቤቱ ከምንኖርበት 3 ማይል ይርቃል (የመጓጓዣ አማራጮች መፈለግ አለብኝ) | 3 |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |



ጥያቄ አለዎት? የተማሪ ማመልከቻውን ለማዘጋጀት እርዳታ ያስፈልግዎታል? በ MY SCHOOL DC የእርዳታ መስመር በ202-888-6336 በመደወል በሚፈልጉት ዕርዳታ ቋንቋ መጠይቅ ይችላሉ፣ ወይም በኢሜል info.myschooldc@dc.gov በመጠየቅ  እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።

# ያመልክቱ

ለማመልከት ምን ያስፈልግዎታል? ☑

- ☐ መጀመሪያ፣ My School DC Family አካውንት በ MySchoolDC.org ድህረ ገጽ ይፍጠሩ።
  ለአዲስ ትምህርት ቤት ለሚያመለክቱ ለእያንዳንዱ ልጅ አ የቤተሰብ አካውንት ይፍጠሩ።

  የኢሜል አድራሻ መስጠት ወይም የተጠቃሚ ስም( username) ፈጥረው የመግቢያ ቃል (password) ማስገባት ያስፈልግዎታል። የMy School DC ማመልከቻ ለማስገባት ቤተሰቦች በየዓመቱ አዲስ የቤተሰብ አካውንት መፍጠር አለባቸው። በየዓመቱ አንድ ዓይነት የኢሜል አድራሻ ወይም የተጠቃሚ ስም መጠቀም ይችላሉ።
- ☐ ቀጥሎም፣ የMy School DC ሎተሪ ማመልከቻውን ይጀምሩ።
  MY SCHOOL DC ማመልከቻ ቅጽ በተሟላ መልኩ አስተካክለው ይቀርቡ ዘንድ የሚመለከቱትን ነጥቦች አሟልተው መቅረብ ይኖርብዎታል።
  - ስለ እያንዳንዱ ልጅ የተሟላ ገለጻ ማድረግ፤
    - ☐ ስም፤የተወለደበት ቀን እና ዓ፡ም፤የትምህርት ደረጃው፤ -አዲስ የተጨመረ! የልጅዎ የተማሪነት መታወቂያ ቁጥር፤በአሁኑ ወቅት የሚማርበት ትምህርት ቤት፤
    - ☐ የተማሪነት መታወቂያን አስመልክቶ ከሚከተሉት ሶስት አይነቶች አንዱን ከመለሱ በቂ ነው።
      - ሀ. ልጅዎ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤት DC Public Schools (DCPS) ተማሪ ከሆነ ይህንኑ የሚያስርዳ መታወቂያ፤
      - ለ. ልጅዎ በህዝብ የሚተዳደር ትምህርት ቤት ተማሪ ከሆነ ይህንኑ የሚያስረዳ ልዩ የተማሪነት መለዮ ያለው መታወቂያ፤
      - ሐ. ሁለቱም የለዎትም? የDC One Card ቁጥርዎን ይጠቀሙ ወይም በስልክ ቁጥር (202) 888-6336 ይደውሉ።
  - ስለቤተሰብዎ መሠረታዊ መረጃ
    - ☐ የአሳዳጊ ስም (የመጀመሪያ እና የመጨረሻ)
    - ☐ አድራሻ መረጃ፣ የአሳዳጊ የመኖሪያ አድራሻዎን ጨምሮ
  - የትምህርት ቤት ምርጫዎች
    - ☐ እስከ 12 ትምህርት ቤቶች መምረጥ ይችላሉ።
    - ☐ የመጀመሪያ ምርጫዎን ይግለጹ (በበለጠ የሚፈልጉትን ትምህርት ቤት)፣ ቀጥሎ ሁለተኛ ምርጫዎን፣ ወዘተ...

## ጥቆማ፤

- ★ የልጆችዎ ማመልከቻዎች በሙሉ በአንድ የቤተሰብ አካውንት ውስጥ መሆኑን ያረጋግጡ።
- ★ የተማሪ መታወቂያ ቁጥር መሙላት የሚያስፈልገው ልጅዎ በአሁኑ ወቅት የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤት ወይም ደግሞ በዲሲ የቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር ከሆነ ብቻ ነው።
- ★ ምርጫዎችዎን በሚፈልጉት ቅደም ተከተል ማስቀመጥ ጠቃሚ ነው። ያስታውሱ: ልጅዎን መስደድ የሚፈልጉባቸውን ትምህርት ቤቶች ብቻ ይዘርዝሩ።

ምርጫዎችዎ በሚፈሉጉት ቅደም ተከተል መዘርዘራቸውን ያረጋግጡ። ተማሪዎች ለአንድ ትምህርት ቤት ብቻ መመደብ እና ከተመደቡበት ወይም ከተመዘገቡበት ትምህርት ቤት በላይ ክፍተኛ ውጤት ላገኙበት ትምህርት ቤት በመጠባበቅ ላይ ይሆናሉ። በማመልከቻው ላይ ማንኛውንም እርማት እስከ ማብቂያው ቀን ድረስ ማድረግ ይችላሉ፡፡

## ያመልከቱ

### በከተማይቱ ከሚገኙ የተወሰኑ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዘንድ ለማመልከት፤

ወንድ ወይም ሴት ልጅዎ ከተማ አቀፍ ለሆኑ የተወሰኑ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች DC Public Schools (DCPS) 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማመልከት ይፈልጋሉን? እንዲያ ከሆነ እኚህ ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ የመግቢያ መመዘኛ ይፈልጋሉ፡ ስለሆነም የሚከተሉትን መረጃዎች አሟልቶ ማቅረብ ይኖርብዎታል። በሚያስገቡት ማመልከቻዎ ውስጥ፤

- PARCC ውጤቶች በሂሳብ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነ ጥበብ (ELA)
- የ2015-16 ትምህርት አመት የመጨረሻ ሪፖርት ካርድ፤
- የ2016-17 የትምህርት አመት ወቅታዊ ሪፖርት ካርድ፤
- ድርሰት( በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች የሚፈልግ)፤
- አስተያየቶች (ለአንዳንድ ትምህርት ቤቶች) ለሚሰጥ አስተዳዳሪ፣ አስተማሪ፣ እና አማካሪ የኢ-ሜል አድራሻ

**ጥቆማ፤**

ተማሪዎች፣ ድርሰት ሲያዘጋጁ የፊደላት ግድፈቶችን እና የቃላቶችን ብዛት ለማስወገድም ሆነ ለማወቅ ድርሰቱን በወርድ ይጻፉት። ድርሰቱ የ5000 ፊደሎች ውስን አለው። የተዘጋጀውን የድርሰት ጽሁፍ ኮፒ አድርገው ማመልከቻው ላይ ያስገቡ።

አባክዎን በትክክል ለመገዝብ ይችሉ ዘንድ ትምህርት ቤቶቹን ለመምረጥ የሚያስችልዎትን የሚከተሉትን ነጥቦች ጠንቅቀው ይረዱ፣ እንዲሁም ለበለጠ መረጃ "How to Apply" የሚለውን በ MySchoolDC.org ድህረገጽ ይመልከቱ።

| | ዝቅተኛ GPA / ዝቅተኛ ውስን የፈተና አስፈላጊ ነገሮች | ድርሰት** | አንድን ተማሪ ለመቀበል የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች፤ | የጽሁፍ ደብዳቤዎችን አስመልክቶ የሚጽፉት አስተያየቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፤የተማሪው፤ |
|---|---|---|---|---|
| **Banneker** (9th-10th) | ዝቅተኛው 3.0 GPA "በቂ"ወይም "ከሚፈለገው በላይ" ውጤት በሂሳብ እና ንባብ በማንኛውም የተወሰነ ፈተና | አዎ ያስፈልጋል፤ | የቀረቡ ማመልከቻዎችን መገምገም፤; የተማሪውን የቤተሰብ አቅም መገምገም፤ | የእንግሊዘኛ መምህር፤; የሂሳብ መምህር፤; የተማሪዎች ጉዳይ አማካሪ፤; የትምህርት ቤቱ ዋና ድሬክተር (ርእስ)፤ |
| **CHEC** (9th-12th) | ምንም የለም፤ | አያስፈልግም፤* | የቀረቡ የተማሪ ማመልከቻዎችን መገምገም፤; በቡድን ቃለ መጠይቅ | የእንግሊዘኛ መምህር፤; የሂሳብ መምህር፤; የተማሪዎች ጉዳይ አማካሪ፤ |
| **Ellington** (9th-10th) | ምንም የለም፤ | አዎ ያስፈልጋል፤ | የቀረቡ የተማሪ ማመልከቻዎችን መገምገም፤; ማመልከቻዎቹ በአጣሪ አካል እንዲታዩ ማድረግ፤; የመግቢያ ፈተና መስጠት፤; ለተማሪው ቤተሰብ የሚደረግ ቃለ መጠይቅ፤ | የእንግሊዘኛ መምህር፤; የሂሳብ መምህር፤; የኪነጥበብ መምህር፤ |
| **McKinley** (9th-10th) | ዝቅተኛ 2.75 GPA በ 4 ዋና ክፍሎች (እንግሊዝኛ፣ ሁሳብ፣ ሥነ ፍጥረት፣ ማህበራዊ ተማሪዎች); 3.0 ተመራጭ "በቂ" ወይም "ከሚፈለገው በላይ" ውጤት በሂሳብ እና ንባብ በማንኛውም የተወሰነ ፈተና | አዎ ያስፈልጋል፤ | የቀረቡ የተማሪ ማመልከቻዎችን መገምገም፤; በቡድን ቃለ መጠይቅ | የእንግሊዘኛ መምህር፤; የሂሳብ መምህር፤; የተማሪዎች ጉዳይ አማካሪ፤ |
| **Phelps** (9th-11th) | ዝቅተኛ 2.4 GPA "በቂ"ወይም "ከሚፈለገው በላይ" ውጤት በሂሳብ እና ንባብ በማንኛውም የተወሰነ ፈተና 95% ወይም በላይ የክፍል ተሳትፎ" | አዎ ያስፈልጋል፤ | የተማሪ ማመልከቻዎችን መገምገም፤; የተማሪ ቤተሰቦችን ለቃለመጠይቅ ማቅረብ፤ | የእንግሊዘኛ መምህር፤; የሂሳብ መምህር፤; የተማሪዎች ጉዳይ አማካሪ፤; የትምህርት ቤቱ ዋና ድሬክተር (ርእስ)፤ |
| **School Without Walls** (9th-12th) | በዋና ትምህርቶች ቢያንስ 3.0 GPA ማግኘት፤ | አያስፈልግም፤ | የተማሪውን ማመልከቻዎች መገምገም፤; የተማሪ የመግቢያ ፈተና መስጠት፤የተማሪው እና የቤተሰብ ለቃለ መጠይቅ" | ምንም የለም፤ |

* የዳሰሳ ጥናቱ ላይ ፍላጎት ያለው ተማሪ ይፈለጋል። ** የጽሑፍ ጥያቄዎች እና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች በMySchoolDC.org ላይ ሊገኙ ይችላሉ።



ጥያቄ አለዎት? የተማሪ ማመልከቻውን ለማዘጋጀት እርዳታ ያስፈልግዎታል? በ MY SCHOOL DC የእርዳታ መስመር በ202-888-6336 በመደወል በሚፈልጉት ዕርዳታ ቋንቋ መጠይቅ ይችላሉ፣ ወይም በኢሜል info.myschooldc@dc.gov በመጠየቅ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።



## ይመዝገቡ

ውጤትዎን ሲያገኙ ምን ያደርጋሉ?

የሎተሪ ውጤቶች ሚያዝያ 1 ቀን 2016 ዓ.ም. ይፋ ይሆናሉ። የሎተሪ ውጤቶችዎን እና የመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ ያለዎትን ውጤቶች ለማየት በ My-SchoolDC.org ድህረ ገጽ ይመልከቱ።

በሎተሪ ለአንድ ትምህርት ቤት ተመድበው ከሆነ፣ በትምህርት ቤቱ ለመግባት እስከ ግንቦት 1 ቀን 2017 ዓ.ም. ድረስ ጊዜ አለዎት። ምዝገባው የሚካሄደው በትምህርት ቤቱ ውስጥ ነው። ልጅ/ቷ በተመደቡበት ትምህርት ቤት ወላጅ ወይም አሳዳጊ በአካል ማስመዝገብ አለባቸው። በተመደቡበት ትምህርት ቤት መመዝገብ በመጠባበቅ ዝርዝር ላይ ካሉት ትምህርት ቤቶች አይሰርዝዎትም።

ለመመዝገብ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፣

- የዲሲ ኗሪ መሆንዎን ማረጋገጥ። የቤትዎን አድራሻ ለማረጋገጥ የሚጠቀሙባቸውን ሰነዶች ዝርዝር በMySchoolDC.org ድህረ ገጽ ይመልከቱ፡፡
- የትምህርት ቤትዎን ተጨማሪ መመዝገቢያ ጥያቄዎች ይከታተሉ።
- የMy School DC መመዝገቢያ ቅጽ ያስገቡ። ቅጹን ከMySchoolDC.org ዳውንሎድ ያድርጉ።

በማብቂያው ቀን ያልተመዘገቡ ቤተሰቦች ከትምህርት ቤቱ ቦታቸውን ያጣሉ።

የሎተሪ ውጤቶችን እና የመጠባበቂያው ዝርዝር እንዴት እንደሚሠራ መረጃ ለማግኘት ወደ MySchoolDC.org ድህረ ገጽ ይሂዱ።

# ይማሩ ❖ ያመልክቱ ❖ ይመዝገቡ

## መስተዋል ያለባቸው ቀናት

ታህሳስ 10 ቀን 2016 ዓ.ም. | EdFEST – ከተማ አቀፍ የህዝብ ትምህርት ቤት ትይይንት

ታህሳስ 12 ቀን 2016 ዓ.ም. | የMy School DC ማመልከቻ ይጀምራል

የካቲት 2 ቀን 2017 ዓ.ም. | ከ9ኛ አስከ 12ኛ ክፍል ባለው የትምህርት ደረጃ ውስጥ ለመግባት ለሚፈልጉ ተማሪዎች የመጨረሻው የማመልከቻ ማስገቢያ ቀን፤

መጋቢት 1 ቀን 2017 ዓ.ም | ከPK3 - 8ኛ ክፍል የማመልከቻ የመጨረሻ ቀን፤

መጋቢት 31 ቀን 2017 ዓ.ም. | የሎተሪ ውጤቶች ይፋ ይሆናሉ

ግንቦት 1 ቀን 2017 ዓ.ም. | መደበኛው የምዝገባ ማቆሚያ

## ጥያቄዎች አሉዎት? እርዳታ ይፈልጋሉ?


**MySchoolDC.org**

**info.myschooldc@dc.gov**

**202.888.6336**

**@MySchoolDC**

**/MySchoolDC**

**@MySchoolDC**



WE ARE WASHINGTON DC
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

DME
OFFICE OF THE DEPUTY MAYOR FOR EDUCATION